Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

# የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርትን የሚመለከት መግልጫ

**በቅርቡ ጀርመን ኣገር ገብተው ትምህርቱን እንዲማሩ ለተፈቀደላቸው ሰዎች እንዲሁም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ጀርመን ኣገር ለሚኖሩና ትምህርቱን መከታተል ግዴታ ያለባቸው የውጭ ዜጎች**

ውድ የዚህ ኣገር የውጭ ዜጎች፥

በጀርመን የመኖርያ ፈቃድ ሕግ መሠረት በጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ላይ ለመካፈል መብት ኣለዎት ኣለበለዝያ ደግሞ ትምህርቱን እንዲካፈሉ በበላይ ኣካል ይገደዳሉ

## የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ምንድነው?

ኰርሱ በኣጠቃላይ 600 ሰዓታት የቋንቋ ትምህርትንና 45 ሰዓታት የገለጻ ትምህርትን ያካትታል። የቋንቋ ትምህርቱ በ100  በ100 ሰዓታት ተከፋፍሏል። የመጀመሪያዎቹ 300 ሰዓታት መሠረታዊ የቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው ሲሆኑ ተከታዮቹ 300 ሰዓታት ደግሞ የቋንቋ ማጠናከርያ ይሆናሉ።

በቋንቋው ትምህርት ወቅት የጀርመን ቋንቋን ለመናገርና ለመፃፍ ዕለት ተዕለት ለመግባቢያ የሚያስፈልግዎትን ቃላቶችና ኣባባሎች ይማራሉ። ከነዚህም መሐል ጉዳይዎትን ለሚመለከቱ ባለሥልጣናት ሓሳብዎን መግለፅ፣ ከጎረቤትዎና ከሥራ ባልደረቦችዎ ጋር መወያየትና እንዲሁም ደብዳቤዎች መፃፃፍና ፎርሞችን ምሙላት የመሳሰሉ ይገኙበታል።

በገለፃው ትምህርት ወቅት ደግሞ ስለ ጀርመን ኣገር ኣኗኗር ሕግና ሥርኣት ባህልና ታሪክ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ይደረጋል።

ከዚህ ሌላ እንደኣስፈላጊነቱ የሚሰጡ ልዩ የትምህርት ዓይነቶችም ኣሉ። ለምሳሌ ያህል ለሴቶች፣ ለወላጆች፣ ለወጣቶችና እንዲሁም ማንበብና መጻፍ በደንብ የማይችሉ ሰዎች የሚሰጥ የትምህርት ዓይነት ኣለ። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት 945 ሰዓታት ይፈጃል። በፍጥነት የመማር ችሎታ ካልዎት የማይቋረጥ ኮርስ መውሰድ ይችላሉ። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት 430 ሰዓታት ብቻ ነው የሚፈጀው።

የትኛው የትምህርት ዓይነት ለርስዎ እንደሚስማማ ወይም ከየትኛው የትምህርት ክፍል መጀመር እንደሚገባዎት የትምህርት ሰጪው ተቋም በቅድምያ በሚሰጠው ፈተና ይወሰንልዎታል።

## የትምህርቱ መደምደምያ ፈተና ላይ ስለመካፈል

የመደምደምያው ፈተና በትምህርቱ ወቅት ከገበዩት የቋንቋ ትምህርትና በገለፃው ወቅት ከተነሱ ሃሳቦች የተውጣጣ ነው። በፈተናው ኣጥጋቢ ውጤት ካሳዩና የቋንቋ ችሎታዎም ከተረጋገጠ፣ የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ተካፍለዋል የሚል ሰርትፊኬት (Zertifikat Integrationskurs) ያገኛሉ።

ውጤትዎ በቂ ካልሆነ ግን ያገኙት ውጤት ብቻ ተጠቅሶ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

የመደምደምያ ፈተና ላይ ለመካፈል የገንዘብ ክፍያ ኣያስፈልግዎትም።

## በጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ላይ መካፈል የሚያስገኘው ጥቅም

በጀርመን ኣገር የሚኖሩ የውጭ ዜጎች ከኣውሮጳ ማህበር ኣባል ኣገሮች ካልመጡ የመኖርያ ፈቃድ ለማግኘት ኣንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ኣለባቸው። ከነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የጀርመን ቋንቋ ጠንቅቆ ማወቅና የጀርመን ኣኗኗርና የሕግ ሥርዓት መረዳት ዋናኞቹ ናቸው። ስለሆነም የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ተከታትሎ በትምህርት መደምደምያ ፈተና ላይ ኣጥጋቢ ውጤት ማምጣት ለመኖርያ ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ያሟላል። በተጨማሪም በኣጭር ጊዜ የጀርመን ዜግነት እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

KNr. 630.036b BAMF 02/2009 Amharisch

እንደዚሁም በትምህርቱ ወቅት የሚገበየው የቋንቋ ዕውቀት የጀርመን ኣገር የዕለተ ዕለት ኑሮዋን ከማቃለሉም በላይ ሥራ የማግኘት ዕድልዎንም ያሰፋዋል።

## ለጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ስለመመዝገብ

በጀርመን ቋንቋ ኣኗኗር ትምህርት ላይ የመካፈል መብት ሲኖርዎት ወይም መማር እንዳለብዎት ሲገደዱ ይህንን የሚያረጋግጥ ወረቀት በፅሑፍ ከኣውስለንደር ኣምት ወይም ለመተዳደርያ የእርዳታ ገንዘብ ከሚያገኙበት ባለሥልጣን ዘንድ ይመጣልዎታል። ከዚሁ የማረጋገጫ ወረቀት ጋርም በሚኖሩበት ኣካባቢ የሚገኙ የትምህርት ሰጪ ተቋማት ኣድራሻዎች ዝርዝርም ይገኝበታል።

በማረጋገጫ ወረቀት ላይ ይህ በትምህርት የመካፈል እንደሚችሉ የሚያሳውቀው የማረጋገጫ ወረቀት የሚያገለግለው እስከ . . . ይልና፣ የሆነ ቀን ተጠቅሶበታል። ስለሆነም ይህ ቀን ከማለፉ በፊት ቀደም ብለው በትምህርት መስጫ ተቋማት ሄደው መመዝገብ ይኖርብዎታል። የማረጋገጫ ወረቀትኑም በምዝገባ ዕለት ለመዘገብዎት ሰው ይስጡ።

የትምህርት መስጫ ተቋሙ የሚቀጥለው የትምህርት ኮርስ መቼ እንደሚጀመር ያስታውቅዎታል። የሚቀጥለው ኮርስ በተከታታዮቹ ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ መጀመር ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን ሌላ የትምህርት ተቋም ሄደው መሞከር ወይም የተባለው ረዥም ጊዜ የመጠበቅ ኣማራጩ የርስዎ ውሳኔ ይሆናል። ይህ ሲሆን የትምህርት ሰጪው ተቋም የማረጋገጫ ወረቀቱን ሊመልስልዎት ይገባል።

## ትምህርቱን በስርዓት ስለመከታተል

የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ኣላማው ግቡን እንዲመታ በትምህርቱ ላይ በሥርዓት መካፈል ይገባዎታል። ይህም ማለት ከትምህርት ገበታ ሳይቀሩና በትምህርት መደምደምያ ላይ በሚሰጠው ፈተና ላይ ሲሳተፉ ማለት ነው። ትምህርቱን በሥርዓት መካፈል ለመጓጓዝ የሚያወጡት ወጪ እንዲመልስልዎትና የቋንቋ ማጠናከርያውን ትምህርት ደግመው ለመማር ቢፈልጉ እንዲፈቀድልዎት ይረዳዎታል። ትምህርቱን በሥርዓት መከታተልዎን የሚገልጽ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ የትምህርት ሰጪው ተቋም ይሰጥዎታል።

## የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ለመካፈል የሚጠየቅ ክፍያ

ትምህርቱን ለመካፈል በድርሻዎ ለትምህርት ሰጪው ተቋም ኣንድ ኣንድ ኦይሮ (1 Euro) በሰዓት ይከፍላሉ። ይህ ክፍያም ከየኮርሱ መጀመርያ ለ100 ሰዓታት ታስቦ በቅድሚያ መከፈል ይገበዋል። በትምህርቱ ወቅት ለሚቀሩባቸው ሰዓታት ኣልነበርኩም ብለው የድርሻዎን ገንዘብ ማስመለስ ኣይችሉም። የራስዎ ገቢ ከሌልዎት የሚያስተዳድርዎ ሰው ይህን ወጪ መሸፈን ኣለበት።

የመተዳደርያ ገቢዎ ኣነስተኛ ሆኖ ለትምህርቱ በድርሻዎ በክፈል የሚገባዎት ገንዘብ የሚቸግርዎት ከሆነ ቡንደስ ኣምት ከክፍያው ነፃ ሊያደርግዎት ይችላል። ስለዚህ ችግርዎን ኣስመልክተው ለክልልዋ ቡንደሳምት በፅሑፍ ያመልክቱ (ኣድራሻ ከሊስቱ ላይ ይገኛሉ)። ከማመልከቻዎ ጋር ምክንያትዎን (በመረጃ) ያቅርቡ። ይህንን ማመልከቻ በተቻለ መጠን ከምዝገባው ጋር ኣያይዘው ለትምህርት ሰጪው ተቋም ያቅርቡ።

ለመተዳደርያ የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ከሆነና እርዳታውን ኪሚያደርግልዎት ክፍል ለጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት እንዲካፈሉ ተገድደው ከሆነ ለትምህርቱ በድርሻዎ መክፈል ከሚገባዎ ወጪ ነፃ ይሆናሉ። እንዲህ ከሆነ ለቡንደስ ኣምት ማመልከት ኣያስፈልግዎትም። ግን ለመተዳደርያ የገንዘብ እርዳታ መውሰድ ሲያቆሙ ግን ለቡንደስ ኣምት ማሳወቅ ኣለብዎት።

## በድርሻዎ የከፈሉትን ገንዘብ ስለማስመለስ

ከ 08.12.2007 በኃላ ትምህርቱን ተከታትለው በትምህርት መደምደምያ ላይ የሚሰጠውን ፈተና በሚገባ ካለፉ ከከፈሉት ገንዘብ ግማሹ ይመለስልዎታል። ይህ የሚሆነው ግን ትምህርቱን ለመማር ከተፈቀደልዎ ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ትምህርቱን ተከታትለው ፈተናውንም ወስደው በኣጥጋቢ ውጤት ሲያልፉ ብቻ ነው። ገንዘቡ እንዲመለስልዎት ለክልልዎ የቡንደስ ኣምት በደብዳቤ ያመልክቱ።

## የትራንስፖርት ወጪ

ወደ ትምህርት መስጫ ጣብያው ለመመላለስ የሚያወጡት ወጪ የሚመለስልዎት ለትምህርቱ በድርሻዎ ማውጣት ከሚገባዎት ገንዘብ ነፃ የሆኑ እንደሆነ፤ ወይም የመኖሪያ ወጪዎን ከመንግሥት እርዳታ ሰጪ ድርጅት የሚያገኙ ከሆነና እንዲሁም ከዚሁ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቱ በኩል የጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት እንዲከታተሉ የተገደዱ እንደሆነ ነው። ትምህርቱን እንዲከታተሉ በኣውስሌንደር ኣምት በኩል የተገደዱ ከሆነ ለትራንስፖርት ወጪው እገዛ ይደረግልዎታል።

ለማንናውም መማመልከቻ የትራንስፖርት ወጪዎን ከምክንያትዎ መረጃ ጋር ኣያይዘው ለቡንደስኣምት ያቅርቡ። በመሠረቱ የትራንስፖርት ወጪ የሚመለስልዎት ትምህርቱን ያለማስተጓጎል በሥነሥርዓት ሲከታተሉ ብቻ ነው።

## የቋንቋ ማጠናከርያውን ትምህርት ደግሞ ስለመማር

የቋንቋ ፈተና ውጤትዎ ኣጥጋቢ ካልሆነ የመጨረሻዎቹን 300 ሰዓታት (የቋንቋ ማጠናከርያ ትምህርት) እንደገና ደግመው መማር ይችላሉ። ይህን መብት የሚያገኙት ግን ባለፈው የትምህርት ወቅት ትምህርቱን በሥርዓት ከተከታተሉና በፈተናውም ላይ የተካፈሉ እንደሆነ ብቻ ነው።

ከድጋሚው የቋንቋ ማጠናከርያ ትምህርት ብኃላ የሚሰጠው ፈተናም ኣይከፈልበትም።

የቋንቋ ማጠናከርያ ትምህርቱን ደግመው መማር ከፈለጉ ማመልከቻዎን ለቡንደስ ኣምት ያቅርቡ።

## የመማር ግዴታ ላለባቸው ሰዎች የተሰጠ ማሳሰብያ

ከኣውስለንደር ኣምት ወይም የመተዳደርያ ገንዘብ እርዳታ ከሚያገኙበት ክፍል በጀርመን ቋንቋና ኣኗኗር ትምህርት ላይ እንዲካፈሉ የግዳጅ ደብዳቤ ሲደርስዎት በተቻለ ግጥነት ኣካባቢዎ ከሚገኝ የትምህርት ሰጪ ተቋም በመሄድ መመዝገብና ትምህርቱንም በሥርዓት መከታተል ይኖርብዎታል።

ይህንን ካላደረጉ ግን ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው በኑሮዎ ላይ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል።

- የመኖርያ ፈቃድዎን ለማራዘም በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ዕቀባ ሊደረግልዎት ይችላል።
- ለመተዳደርያ የሚያገኙት የእርዳታ ገንዘብ ሊቆረጥብዎት ይችላል።
- ከዚያም በላይ ለትምህርቱ በድርሻዎ መክፈል ያለብዎትን ገንዘብ ሁሉንም በኣንድ ጊዜ እንዲከፍሉ ኣውስለንደር ኣምት ሊያስገድድዎት ይችላል።
- የገንዘብ መቀጫም ሊበየንብዎት ይችላል።

ትምህርቱን በስነ ስርዓት ካልተከታተሉ የትምህርት ሰጪው ተቋም ለኣውስለንደር ኣምት ወይም የመኖርያ እርዳታ ገንዘብ ለሚሰጣችሁ መስርያ ቤት ስለዚሁ ጉዳይ የመንገር ግዴታ ኣለበት።

## ከዚህ ሌላ ማወቅ የሚገባዎት ነገር

⇒ በዚህ መግለጫ ላይ የተጠቀሱት የማመልከቻ ፎርሞችን ከትምህርት ሰጪ ተቋማት፣ ከኣውስለንደር ኣምት ወይም የርስዎን ጉዳይ ከሚመለከተው ክፍል ያገኛሉ። በተረፈም ከኢንተርነት www.integration-in-deutschland.de.

ማመልከቻ መፃፍ፣ ፎርም መሙላትና ከተለያዩ የትምህርት ኣሰጣጥ ዓይነቶች የትኛው ለርስዎ እንደሚስማማ የመምረጥ ችግር ካለብዎት ለስደተኞች ምክርና እርዳታ ከሚሰጡት ድርጅቶች ዘንድ ለመሄድ ለችግርዎ ተገቢውን ምላሽ ያገኛሉ። እነዚህ ድርጅቶች እርስዎን ለመርዳት ሁሌም ዝግጁ ናቸው። በርስዎ የመኖርያ ኣካባቢ እነዚህ መፍትሄና ምክር ሰጪ ድርጅቶች የት እንደሚገኙ ኣድራሻቸውን ከኣውስለንደር ኣምት ወይም ከክልልዎ የቡንደስ ኣምት የበላይ ክፍል ያገኛሉ። ኣለበለዚያም ከኢንተርነት www.integration-in-deutschland.de.